Amharic

# የጥበቃ ደብዳቤ

## የሴት ብልት ትልተላ ጥበቃ

ወደውጪ ሲሄዱ ይህን ደብዳቤ ሁልጊዜ ይያዙ:: የሴት ብልት ትልተላ (FGM) ጀርመን ውስጥወንጀል እንደሆነ ለቤተሰብዎ በግልጽ መንገር እንዲችሉ::

Hamburg

### ጥያቄ አለዎት?

ስለየሴት ብልት ትልተላ ጥያቄ ካለዎት ለሴቶች ጥቃት የብሄራዊ እርዳታ ስልክን በስልክ ወይም ኦንላይን ያነጋግሩ:: የእርዳታ ስልኩ በ17 ቋንቋዎች ምክር ይሰጣል - በቀን 24 ሰአት::

HILFE TELEFON
GEWALT GEGEN FRAUEN
08000 116 016
www.hilfetelefon.de

ይህን ሰነድ ሁሌ ወደውጪ ሲጓዙ ከእርስዎ ጋር እንዲሆን ከጉዞ ሰነድዎት ጋር በጥንቃቄ ያስቀምጡ::

ህትመት
ነጻ እና Hanseatic የ Hamburg ከተማ
የ Hamburg የህዝብ ግንኙነት የስራ መምሪያ፣ የማህበራዊ ጉዳይ፣
የቤተሰብ እና ውህደት መምሪያ 47, 22083 Hamburg

መላኪያ አድራሻ፡
Behörde für Arbeit, Soziales, Familie und Integration
Zentraler Broschürenversand
ስልክ፡ 040/428 63-7778
ኢሜል: publikationen@basfi.hamburg.de

### የሴት ብልት ትልተላ (FGM) ምንድን ነው?

የሴት ብልት ትልተላ ወይም FGM የሴት ብልት ውጪኛው ክፍል ለህክምና ባልሆነ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መቆረጥ ነው:: የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው::

### የሴት ብልት ትልተላ ለጤና በጣም ጎጂ ነው::

FGM ብዙጊዜ የእድሜ-ልክ የጤና ችግር ያስከትላል:: በዚህ ምክንያት ሴት ልጆች በመድማት ወይም በኢንፌክሽን ሊሞቱ ይችላሉል:: በርካታ ሴቶች የእድሜ-ልክ ህመም እና ቋሚ የአካላዊ እና የስነ-አዕምሯዊ ጉዳት:: ለምሳሌ

ሽንት ሲሸና እና በግብረ-ስጋ ግንኙነት ወቅት ህመም፣ መቆጣጠር አለመቻል፣ ከባድ የወር አበባ ችግር እና የፊኛ እና ማህጸን ኢንፌክሽን::

ሌላ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡

አለመውለድ፣ በወሊድ ወቅት ችግር ወይም ከባድ ድብርት::

### የሴት ብልት ትልተላ አለማቀፋዊ እና የጀርመንን ህግ ይጥሳል::

**FGM በጀርመን ያስቀጣል:: የሴትን ብልት የውጪኛውን ክፍል የሚተለትል ወይም ለመተልተል የሚሞክር ሰው እስከ 15 አመት ድረስ የሚያስቀጣ እስር ይጠብቀዋል:: ወንጀሉ ሌላ አገር ቢፈጸምም እንኳን ቅጣቱ ይፈጸማል::**

ሴት ልጅ ቤት ውስጥ ወይም ሌላ አገር ብልቷ እንዲተለተል ያደረጉ ወይም ሌሎች እንዲያደርጉ ያበረታቱ ወላጆችም ክስ ይቀርብባቸዋል::

የሴት ብልት መተልተል ወይም ለመተልተል መሞከር የመንግስት ተቋማት ሴት ልጅቷል በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ከወላጆቿ እንዲወስዷት ይፈቅዳል እንዲሁም ወላጆች የሴት ልጃቸውን የማሳደግ መብት ያሳጣል::

በቅጣት ወቅት የጀርመን ዜግነት የሌላቸው ወላጆች በተጨማሪ ጀርመን ውስጥ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የመኖር መብታቸውን ሊያጡ ይችላሉ::

ሴት ልጆች አካላዊ ህልውናቸው ላይ ከሚደርስ ማንኛውም ጥቃት እና አደጋ መጠለያ እና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል:: የእነዚህ ልጆች እና ሴቶች መብቶች ላይ የሚደርስ ጥሰት ቅጣት ማግኘቱን ማረጋገጥ የመንግስት ሀላፊነት ነው::

የስራ፣ የማህበራዊ ጉዳይ፣ ቤተሰብ እና ውህደት ሴናተር

የጤና እና የተጠቃሚዎች ጥበቃ ሴናተር

የፍትህ ሴናተር

የአገር ውስጥ ጉዳይ እና ስፖርት ሴናተር